# በጀርመን አገር በሃምበርግ ከተማና አከባቢው የምንኖር ኢትዮጵያውያን የተሰጠ የሐዘን መግለጫ፣

አምስተኛው ዬኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ፓትርያሪክ አቡነ ፓውሎስ ከዚህ ዓለም ዐርፈው የቀብር ሥርዓታቸው ነሐሰ ፩፺ ቀን ተፈጽማል።

እግዚአብሔር አምላክ ነፍሳቸው በቅዱሳን ጎን ያሳርፍ ዘንድ እንፀልያለን።

እንዲሁም ዬኢትዮጵያ ፈደራላዊ ሪፓብሊክ ጠቅላይ ሚኒስተር ክብር አቶ መለስ ዜናዊ ከወጣትነት ዕድሜያቸው ጀምሮ እስከ ዕለተ ህልፈታቸው ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና እኩልነት፣ ለዴሞክራሰያዊና ፈደራላዊ ሥርዓት መገንባት ከሌሎች የትግል ጋዶኞቻቸው ጋር በመሆን በአላማ ጽናት ከተራ ታጋይነት እስከ መሪነት በመታገልና በማታገል ጠንካራ ድርጅት በመመስረት በሀገራችን ጥሩ የሚባል የዲሞክራሲ መሰረት እንዲገነባ ትልቅ አስተዋፀኦ አድርገዋል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ አገራችን ኢትዮጵያ የነበራት የኃላቅሪነት ገፅታ ለመቀየርና የህዝቦቿን ያኗኗር ሁኔታ ለማሻሻል ለግል ኑረአቸውና ለህይወታቸው ሳይሳሱ ያለዕረፍት ሌት ተቀን ሲሰሩ በመቆየታቸው፣ በመጨረሻ በሞት ተለይተውናል። ሆኖም ግን የተጀመሩትን ታላላቅ ስራዎች ለመፈጸም ሁላችንም የበኩላችን እያደረግን በውጤቱም እሳቸውን የምንዘክርበት ነው።

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ህዝብና ለቤተሰባቸው መጽናናት እንዲሰጥልንና ነፍሳቸውንም በገነት ያኑርልን ዘንድ እንጸልያለን።

ነሐሴ ፩፺ ሃምቦርግ